# ብርቱካንን እንጂ አላማውን ማሰር አይቻልም!!!

## በስዊድን የተካሄደ ብርቱካን ትፈታ ህዝባዊ ስብሰባ

ከስሜነህ ታምራት (ስዊድን)

20 february 2010

Stockholm

የመሰብሰቢያ አዳራሹ በኢትዮጵያና በስዊድን ሰንደቅ አላማዎች ከብርቱካን ፎቶግራፍ ጋር ተውበዋል። ወደ ውስጡ ሲገባ ብርቱካን ቃሌ ብላ ከሰጠችው የተወሰደው የእውነተኛ ምስክርነት ንግግርና ለእስር ምክንያት ተብሎ የቀረው በስዊድን ጉብኝትዋ ስለምህረቱ አፈፃፀም ያደረገችው ንግግር ይሰማል። በተለያዩ ሃገሮች ከህዝብ ጋር ስትወያይ "ባገራችን ሰላም ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት እንዲከበር እኔ በአላማዬ ፅኑ ነኝ እናንተስ?" በማለት ያስተላለፈችውና በማንኛውም ዜጋ ጋር ዘወትር የማይረሳው የቆራጥነት መንፈሷ በአየር ላይ ይታያል።

ሻምበል እኛስ ኮራን በብርቱክን በማለት መታሰብያነቱን ለዚች እንቡጥ እስረኛ ያዜመው  ጣእመ ዜማ በንግግሮቿ ጣልቃ ይደመጣል። ወደ አዳራሹ ሲገቡና የእሷን ንግግር ሲሰሙ እንባ ያዘሉ አይኖች በርካታ ነበሩ። "ኢትዮጵያ ሀቀኛ ልጆች እስከመቼ ነው የአምባገነኖች እሳት የሚለበለቡት" እያሉ በቁጭትም ተናግረዋል።

የአንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ዳኛ ወይዘሪት ቢርቱካን ሚደክሳ ለሁለተኛ ጊዜ ታስራ በስቃይ ላይ መሆንዋን በማስታወስ በስዊድን የትፈታ ትግሉን ለማጠንከር ስቶክሆልም ኤቢኤፍ አዳራሽ  FEB 20, 2010 ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ።

ወይዘሮ ብርቱካን ሚደቅሳ የዛሪ አመት በታህሳስ ወር በአውሮጳ ጉብኝትዋ በተለይ በስዊድን ላይ ባደረገችው ንግግር መንግስት የሰጠሽን ምህረት ክደሽ በምህረት አልወጣሁም ብለሻልና ይህን ቃልሽን አስተባብለሽ መግለጫ ስጪ ትባላለች። ብርቱካን ግን የማስተባበያ መልሷን እንድትሰጥ ከተሰጣት ጊዜ ቀድማ "ቃሌ" በሚል ርዕስ  ከተማረችው የህግ ሙያ አንፃር የይቅርታ አሰጣጡን አመልክታ የተናገረችውን እንደማትለውጠው የጋዜጣዊ መግለጫ ትሰጣለች።

ይህ ንግግሯ ድፍረቷ ሞራሉን የነካው የመሰለው እብሪተኛ መንግስትም በፀጥታ ሃይሎች እያዋከበ ቃሊቲ እስር ቤት ከወረወራት አንድ አመት አልፍዋል።

ስዊድን የሚገኘው የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ማህበር ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ፕሮግራሙ የተጀመረው አንድ ወጣት ስለ ብርቱካን እንባ እየተናነቀው ባሰማው ግጥምና በሶስት ደቂቃ የህሊና ፀሎት ነበር።

በመቀጠልም ስብሰባውን የመሩት አቶ ታምራት አዳሙ በኢትዮጵያ ያለው የአንባገነናዊ ስርአት ገላጭ ባህሪያት ከገለፁ በህዋላ ፕሮግራሙን በማስተዋወቅ የስዊዲን የድጋፍ ማህበር ሊቀመንበር የመግቢያ ንግግር እንዲያደርጉ ጋበዙ።

አቶ ራስ-ወርቅ መንገሻ የስዊድን የድጋፍ ማህበር ሊቀመንበር ባደረጉት ንግግር ባደረጉት ንግግር በኢትዮጵያ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጭራሹኑ አየታፈኑ እንደመጡና አብሪተኛው መንግስት ወይዘሪት ብርቱካንን በማሰር የተቀጣጠለውን ህዝባዊ አመፃን ማፈን እንደማይቻልና እንዲሁም ትግሉን በነፃነት ህልውና እንደሚቀጥል ገልፀው ብርቱካንና መላው የፖለቲካ እስረኞች የማስፈታት ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

አገር አቀፍና አለም አቀፍ ዜናዎች ለኢትዮጵያውያን በሬድዮ በማቅረብ ጎበዝ ሚና የሚጫወተው በስዊድን የኢትዮጵያ ድምፅ አዘጋጅና የኢትዮጵያዊያን ማህበር ኮሚቴ ሊቀመንበር አቶ አህመድ አሊ በበኩሉ እንዲህ ሲል ንግግር አሰምትዋል። ኒልሰን ማንደላ ታስሮ በነበረበት ወቅት በግንባር ከተሰለፉት ሃይሎች ስዊድኖች የመጀመሪያዎቹ መሆናቸውና ማንዴላ ከነፃነት በህዋላ ስዊዲንን ሲጎበኙ መስክረዋል።

ይህም የቀድሞውን የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስቴር ጨምሮ ብዙ ስዊድናውያን እጅግ እንደኮሩ ገልጠዋል። ዛሬ ለእኛዋ ብርቱካንም የሚደረገው እገዛም ወደፊት ተመሳሳይ ታሪክ እንደሚኖረው ገለፁ። መላው የስዊዲን የፓርቲና የፓርላመንት ባለስልጣናት ብርቱክን ሚደክሳና ሌሎችም የፖለቲካ እስረኞችም እንዲፈቱ ተግባራዊ ግፊት እንዲያደርጉ ጥሪውን አቅርብዋል።

በመቀጠልም ንግግር ያደረጉት የአውሮጳ 60 ሚሊዮን ሰራተኞች የሚወክሉትና የአውሮጳ የሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር የሆኑት ቫኒያ ሉንዲን ናቸው። እሳቸውም የኢትዮጵያንና የስዊዲንን የረጂም ጊዜ ግኑኝነት ገልው ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው የሰራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን ራሱ ምንም ነፃነት እንዳሌለውና በሃገሪቱ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በእጅጉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙና ይህን ለመለወጥ የትግል አንድነት ኣአስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል። አያይዘውም አምንስቲ ኢንተርናሽናል ብርቱካን ሚደቅሳን አስመልክቶ ያወጣውን መግለጫ በእንግሊዝኛ በንባብ ካሰሙ በህዋላ በሃሳቡ መቶ በመቶ እንደሚስማሙና ትግላቸውም እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል።

የተከበሩ ሚስስ ቫኒያ ሉንዲን የአውሮፓ የሰራተኛ ማህበር ሊቀ-መንበር በአውሮፓ ህብረት ውስጥ ከአና ጎሜዝና ከግሪታ ኦልስኮግ በመሆን በኢትዮጵያ ያለውን ኢ-ሰብአዊና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ስርአት በማጋለጥ ከኢትዮጵያዊያን ጎን ተሰልፈው ለሰላም፣ ለፍትህና ለዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲሁም ለብርቱካንና መሰል የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በህብረት እንደሚታገሉ ይጠበቃል።

በስዊዲን የሚገኙ እናቶችና እህቶች ከዚህ ቀደም ለብርቱካን ቤተሰብ መርጃ የሚሆን የእራት ዝግጅት አድርገው የድርሻቸውን መወጣታቸው ይታወሳል።

በዚህ ታሪካዊ ”የብርቱካን ትፈታ” ህዝባዊ ስብሰባ ላይም ሴቶችን በመወከል ወይዘሮ የሺ ወንድሜነህ በኢትዮጵያ ከፍትህ ማጣት የተነሳ የሴቶችን ጣምራ ችግርና መፍትሄውም መልካም አስተዳደር መሰረት መሆኑን ገልፀዋል። ወይዘሮ የሺ ከዚህ ቀደም ካሳተምዋቸው መፃህፍት 20ዎቹ ተሽጠው ገቢው ለብርቱካን ቤተሰብ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት እንዲዉል ያደረጉና የወጣት ሴቶችን ትግል የሚያበረታቱ ጠንካራ ኢትዮጵያዊት ናቸው። በዚህ አጋጣሚ ሌሎችም በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸው እህቶቻችን እንደ ወይዘሮ የሺ ወንድሜነህ ምሳሌነታቸውን ተግባሪዊ በሆነ አስተዋፆ እንዲያደርጉ ብዙ ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ የብርቱካን እስር አንደኛ አመት የትግል መግለጫ/solidarity/ እና የብርቱካን ትፈታ /free Birtukan/ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ በጥበብ ስራቸው በተለያዩ ድህረ ገፆች የሚታወቁት መስከረም አየለና ማቲያስ ከተማ እሪ አለች ምድሪትዋ እና ብርቱካን ትፈታ በሚሉ ርዕሶች የግጥም ዝግጅቶች በማቅረብ ለስብሰባው ታላቅ ክብር አላብሰውታል። እኛም አለን በተጠንቀቅ የሚሉ የአንድነት ወጣቶችን በመወከልም ወጣት ብርሃኑ ወጣት ታጠቅ የብርቱካን ትፈታ እጭር ግጥማቸውን አሰምተዋል።

ዳኛ ብርቱካን ሚደክሳ በአዲስ አበባ የዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርትዋን አጠናቃ ከተመረቀች በህዋላ በሞያዋ የህግ የበላይነትን በሃገሪትዋ ለማስከበር ከነበራት ቀና ራዕይ ተነስታ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ሰርታለች። ይሁን እንጂ የገዢው ፓርቲ ሆድ አደር ዳኞችን እየተጠቀመ ወገኖችና ተቃዋሚዎችን በሚጎዳበት የጥፋት ተግባር ፊፅሞ ባለመስማምዋቷ የዳኝነት ስራዋን ለመተው ተገዳለች።

ይህ ዛሬ ካለንበት ዘመን አክዋያ እጅግ ሁዋላ ቀርና ጠንቀኛ የሆነ የጎሳ ፖለቲካ አራማጅ መንግስት በሃገሪቱና በዜጎቹ ላይ የሚፈፅመውን የእኩይ ተግባር ለመቃወምም ከተቃዋሚዎች ጎሳ ተሰልፋ በግልዋ ፓርላመንታዊ ተወዳዳሪ ሆና ነበር። ሆኖም ቀድሞ ቅንጂት የነበረው ምርጫ ሙሉ በሙሉ በወያኔ እጅ ስለነበር ያሰበችው አልተሳካላትም። በዚህ ጊዜ ነው የቅንጂት መስራች አንድ አካል የነበረውን የቀስተ ዳመናን ፓርቲ በመቀላቀል የተናጥል ትግልዋን ወደ ድርጅታዊ ትግል ያሳደገችው።

ብርቱካን በነበራት የለውጥ ፈላጊነትና ስሜትምና በምታቀርባቸው ሃገራዊ ጉዳዮች /National values/ በወጣቶች ብቻ ሳይሆን ወልደው በሚያደርሷት የዕድሜ ባለፀጋ ኢትዮጵያውያንም ታላቅ ክብርና ተወዳጅነትን እያገኘች መጣች። ለዚሁም ነው በአጭር ጊዜ የቅንጅት ምክትል ሊቀ-መንበር ለመሆን የቻለችው።

በሃይል ከተነጠቀው ታላቁ የግንቦት ምርጫ በህዋላ ለሁለት አመታት ያህል በእስር ከቆየች በህዋላም እንደተፈታች ቅንጅት በልዩ ልዩ ምክንያቶች በቅንጅትነት ለመቀጠል ያልቻለበት ሁኔታ ሲፈጠር ህዝባዊ አላማውን አንግባ ከመስል የትግል አጋሮቿ ጋር አንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ፓርቲን መስርታለች።

በሃገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያዋ የሴት መሪ ሆና በቅንጅት ዓላም በአንድነት መንፈስ በእግሩ አቁማ ህዝባዊ ዓላማውን ለማሳካትም ቅርጣ ተነሳች። ይህን አደገኛ የሚለውን እንቅስቃሴ በስጋት የተመለከተውና ዕረፍት ያጣው የኢህአዴግ መንግስት ይህችን ወጣት፣ አንስታይ፣ የህግ ባለሙያና የልጅ እናት በተለጣፊ ሰበብ በድጋሚ አሰራት። አዎ ብርቱካንን አስሯታል። የብርቱካንን አይበገሬ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ግን ማሰር አይቻልም። እንዳውም እሷን ማሰሩ ተከታታይ ዓለም አቀፍ ውግዘትን፣ ለእርስዋ ደግሞ ክብር ፅናትን አጎናፀፋት።

ብርቱካንን በማሰር ወያኔ ፖለቲካዊ ኪሳራን አስከትሎበታል። ለዚህ ነው ዛሬ በብርቱካን ዳግማዊ እስር የራሱ የወያኔ አባላት ሳይቀር የተለያየ አስተያየት የሚሰጡት። ዛሬ በተበበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ጉዳይ ሳይቀር ብርቱካን ያለ አግባብ ታስረው ከሚገኙ በርካታ ዜጎች አንዷ መሆኗን ገልፆ መግለጫ አውጥተዋል። ይህ መግለጫ በራሱ የወያኔ መንግስት ብርቱካንን በፖለቲካ ምክንያት እንዳሰራት ታላቅ ማስረጃ ነው።

በውጭ ያለው የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ ጩኸት አስሚ ወገን ሁሉ በያለበት ሀገር በየጊዜው የብርቱካን ትፈታ ጥያቄውን ማስተጋባቱ የብርቱካን ዓላማ አብሯት እንዳልታሰረ ያበስራል። አዎ ብርቱካን ታስራለች። አንድ ወላድ እናት አዝናለች። የእናት ፍቅር ያጣችው ሐሌም ታለቅሳለች። የብርቱካን የነፃነት ራዕይ ግን አሁንም የብርሃን ዘመንን እያመለከተ የብርሃን ፋና እያበራ ይገኛል። የብርቱካንና የመላው ኢትዮጵያዊያን የነፃነት ቀንም ሩቅ አይሆንም። በሰፈሩት ቁና መሰፈርም አይቀሬ ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ይሏል። ብርቱካን እንድትፈታ የምንታገለው ብርቱካን በእናትነቷ የልጅ አሳዳጊ እንድትሆን አይደለም። ብርቱካን ዛሬ በሃገራችን ከሚታየው የፖለቲካና የፖለቲከኞች መዋዥቅ አንፃር ያላት ቆራጥ አቋዋምና የመሪነት ብቃት/Leadership quality/ አንፃር ትክክለኛ የሃገር መሪ መሆን የምትችል አርማችን በመሆኗ ነው። የአንድነት ትግሉም የጋራ ድሉም ይቀጥላል …።

ብርቱካን ታስራለች አላማዋ ግን አልታሰረም። አላማዋ ግን አልታሰረም። በነፃነት ከዓለም አለም ከአጥናፍ አጥናፍ የነፃነት ድምፅ እያሰማ በአንድነት እንታገል በአንድነት እንታገል በአንድነት ነፃ እንውጣ ይላል።